GSMA

# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

## ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

# ሞጁል 1፡- ስለ በይነመረብ መግቢያ

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ


ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

አጭር ሥልጠና፦

# ስለ በይነመረብ መግቢያ

ይህ ገጽ ስለ ተንቀሳቃሽ ስልክ በይነመረብ ሰልጣኞች የሚያነሷቸውን አጠቃላይ ጥያቄዎች እንዲመልስ ለመርዳት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ሰዎች ስለ በይነመረብ ብዙ ጊዜ ለሚጠይቋቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ቀላል ማብራሪያዎችን ይሰጣል። ይህን ሉክ ማተም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም እነዚህን ምሳሌዎች በዚህ የመርጃ ስብስብ ሞጁሎች ውስጥ ያገኟቸዋል።

## ይህ ምንድን ነው?




**«ስለ በይነመረብ መግቢያ» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

**ያብራሩ፦** «በይነመረብ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ እርስ በርሳቸው በስልክ መስመሮች፣ በሳተላይቶች እና በመረጃ ገመዶች የተያያዙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኮምፒውተሮች ያሉት መረብ ነው። ዘርፈ ብዙ መጠን ያላቸው መረጃዎችን እና አገልግሎቶችን ለመጠቀም ይረዳዎታል፣ ይህም በየጊዜው ዕድገት እያሳየ ይገኛል። በይነመረብ ሁሉም ሰው እንዲጠቀምበት የተዘጋጀ ነው። ማን ሊጠቀምበት እንደሚችል ምንም ገደብ የለውም። የሚያስፈልግዎት ኮምፒውተር፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም ታብሌት እና የአየር ሰዓት ግንኙነት ብቻ ነው።»

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

«በይነመረብ ብዙ ነገሮችን እንዲያደርጉ ሊረዳዎት ይችላል፦

- የንግድ ሥራዎን እንዲያስተዳድሩ፣ ከደንበኞች እና አቅራቢዎች ጋር እንዲገናኙ እንዲሁም በቀላሉ ከቤትዎ ሆነው ንግድ እንዲሰሩ እና የሚያደርጉትን ጉዞ እንዲቀንሱ።
- መልዕክቶችን እና ፎቶዎችን እንዲልኩ እንዲሁም ርቀው ከሚኖሩ ቤተሰብ እና ጓደኞች ጋር እንደተገናኙ እንዲቆዩ።
- ቪዲዮዎችን፣ ሙዚቃዎችን እና ስፖርቶችን በመመልከት እየተዝናኑ እንዲቆዩ።
- የቅርብ ጊዜ ምርቶችዎንና አገልግሎቶችዎን ለማስተዋወቅ እና ለመሸጥ ወይም ቤተሰብዎ የሚፈልጓቸውን ነገሮች ለማምረት ወይም ለመግዛት።
- አዳዲስ የምግብ አሰራሮችን፣ የንግድ ሥራ አስተዳደርን፣ የተበላሸ ነገር አጠጋገን፣ ወይም የግብርና ሥራ አሰራሮችዎን ስለማሻሻል እና የመሳሰሉ አዳዲስ ነገሮችን ለመማር።
- እንደ ዜና፣ የአየር ሁኔታ፣ የትራንስፖርት የጊዜ ሰሌዳ፣ የሀይማኖት ትምህርቶች፣ ስለቤተሰብዎ ጤና ምክር እና በመሳሰሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መረጃ ለመፈለግ እና ለማግኘት።

በይነመረቡ ሊረዳዎ የሚችልባቸው ብዙ ሌሎች ነገሮች አሉ። እነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።»

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ለሰልጣኙ ሕይወት እንዴት** ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል በመወያየት ከሰልጣኙ ጋር የሚገናኝ እንዲሆን ያድርጉት። ለሚከተሉት የሰልጣኝ ዓይነቶች ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን ታሳቢ ያድርጉ፦

**አዛውንት፦** መልዕክት በመለዋወጥ ወይም ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ከቤተሰብ ጋር እንደተገናኙ ይቆዩ፤ በመስመር ላይ ስለ ጤና መረጃ ይፈልጉ።

**እናት ወይም የቤት እመቤት፦** እንደ ልብስ መስፋት ወይም ማስተካከል የመሰሉ አዳዲስ ክህሎቶችን ይማሩ፤ ልጆችን በትምህርታቸው ዙሪያ ይደግፉ፤ ስለ ልጅ ህመም ሐኪም ያነጋግሩ።

**የንግድ ሥራ ባለቤት፦** ከደንበኞች ወይም አቅራቢዎች ጋር ይገናኙ፤ የእርስዎን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ያስተዋውቁ ወይም ይሸጡ፤ ስለ ንግድዎ አዳዲስ ነገሮችን ይማሩ፣ ይወቁ።

**ገበሬ ወይም የገጠር ሰው፦** የገበያ ዋጋዎችን እና የገበያ ቦታዎችን፣ የአየር ሁኔታ ትንበያዎችን እና ስለ እርሻ ምርጥ ተሞክሮ መረጃ እና ጠቃሚ ምክሮችን ያግኙ።

**ወጣት**፦ በትምህርት ዙሪያ እገዛ ያግኙ፤ አዳዲስ ነገሮችን ይማሩ እንዲሁም ስለሚወዱት ሙዚቀኛ ወይም ስፖርተኛ ቪዲዮዎችን በመመልከት እየተዝናኑ ይቆዩ።


## እንዴት ነው የሚሰራው?

### በይነመረብን ለመጠቀም ሁለት ዓይነት ተንቀሳቃሽ ስልኮች አሉ።

**ስማርት ስልኮች፦** «እነዚህ ስልኮች እንደ አነስተኛ ኮምፒውተሮች ናቸው። በተለምዶ አዝራሮችን ከመጠቀም ይልቅ ስክሪኑን በመንካት ይቆጣጠሯቸዋል። ፎቶዎችን ማንሳት፣ ሙዚቃ እና ቪዲዮ ማጫወት ይችላሉ እንዲሁም በፍጥነት ወደ የበይነመረብ አገልግሎት የሚወስዱ መተግበሪያዎች አሏቸው።»

**መደበኛ (ፊቸር) ስልኮች፦** «እነዚህ ከስማርት ስልኮች አንፃር ያነሱ አገልግሎቶች ያሏቸው ናቸው። ሊነኩት የሚችሉት ስክሪን የላቸውም ነገር ግን ሙዚቃ ማጫወት እና ፎቶዎችን ማንሳት ይችላሉ። የሚፈልጉትን የመስመር ላይ አገልግሎቶች ለመጠቀም በአሳሽ አማካኝነት በይነመረብ መክፈት ይችላሉ።»

## የአየር ሰዓት ወጪዎች




«በተንቀሳቃሽ ስልክዎ በይነመረብ ለመክፈት የሞባይል ግንኙነት ወይም የዋይ ፋይ ግንኙነት መጠቀም ይችላሉ።»

**«የዳታ ወጪዎች» ፖስተርን ያሳዩ።**

«በተለምዶ በስልክዎ በይነመረብ ሲጠቀሙ የሚጠቀሙት የሞባይል አየር ሰዓት ነው። ይህንን ከአካባቢዎ የሞባይል አውታረ መረብ ወኪል ወይም የአየር ሰዓት ከሚሸጥ ሱቅ መግዛት ይኖርብዎታል።

ቪዲዮዎችን መመልከት ወይም ሙዚቃ ማዳመጥ የመሳሰሉ በበይነመረብ ላይ የሚያከናውኗቸው አንዳንድ ተግባራት የበለጠ አየር ሰዓት ይጠቀማሉ፣ እናም ተጨማሪ ገንዘብ ያስወጡዎታል።»

# ፖስተሮች እና ተቆርጠው የወጡ ማሳያዎች

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

# በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች

**በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ያስታውሱ፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም ራስዎን በመጠበቅ እና በመስመር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።**

## በመስመር ላይ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ያስታውሱ

ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር በመስመር ላይ መለጠፍ ይችላል፣ ስለዚህ የሚመለከቱትን ሁሉ አይመኑ። ከሚያምኑት ሰው እንኳን ቢሆን እውነት ላይሆን ይችላል። መረጃን ለሌሎች ከማጋራትዎ በፊት ጥንቃቄ ያድርጉ።

## በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው ገንዘብ ከመላክዎ በፊት ደግመው ያስቡ

ያልጠየቋቸውን ኢሜይሎች፣ መልዕክቶች ወይም ብቅ-ባዮች በተለይም ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆኑ ወይም እንግዳ የሆኑ አገናኞችን ከያዙ ይጠንቀቋቸው።

## የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ የግል መረጃዎን ለግልዎ ያቆዩ

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር፣ እንደ ሙሉ ስምዎ፣ የቤት አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ያሉ የግል ዝርዝሮች ማጋራት የለብዎትም።

## በመስመር ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት አያድርሱ

መልካምነትን እና አክብሮትን ያሳዩ። ጉልበተኝነት አያሳዩ፣ የውሸት መረጃን አያሰራጩ ወይም ማንም ሰው ላይ ትንኮሳ አያድርሱ። በመስመር ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእውነተኛ ሕይወት ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።


## ማጭበርበሮችን እና አጭበርባሪዎችን ይወቁ

ልክ በእውነተኛ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ በበይነመረብ ላይም ሌቦች እና ወንጀለኞች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በመስመር ላይ ሌላ ሰው እንደሆኑ ያስመስላሉ።


## የሚያስቸግርዎትን ሰው በማገድ ወይም ችላ በማለት እርምጃ ይውሰዱ

የሆነ ሰው በመስመር ላይ ካስቸገረዎ ወይም ትንኮሳ ካደረሰብዎ፣ እርዳታ ይጠይቁ እንዲሁም ለሆነ ሰው ይናገሩ ወይም ሪፖርት ያድርጉ።

# የዳታ ወጪዎች



# ስለ በይነመረብ መግቢያ



## ቤተሰቤን መንከባከብ



«ቢታንያ ቤተሰቧን እና ጓደኞቿን ለመደገፍ እና ለመንከባከብ በይነመረብን ትጠቀማለች»

ንግዴን
መደገፍ



«ኤማን ንግዷን ለመደገፍ እንዲረዳት
በይነመረብ ትጠቀማለች»

## ተጨማሪ ክህሎቶችን መማር



«ቤዛ ተጨማሪ ክህሎቶችን ለመማር
እንዲረዳት በይነመረብ ትጠቀማለች»

## ቤተሰቤን መንከባከብ



**«ብሩክ ቤተሰቡን እና ጓደኞቹን ለመደገፍ እና ለመንከባከብ በይነመረብ ይጠቀማል»**

ንግዴን መደገፍ



«አህመድ ንግዱን ለመደገፍ እንዲረዳው በይነመረብ ይጠቀማል»

# ተጨማሪ ክህሎቶችን መማር



«ተስፋዬ ተጨማሪ ክህሎቶችን ለመማር እንዲረዳው በይነመረብ ይጠቀማል»

ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

## ስለ በይነመረብ መግቢያ



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

## ስለ በይነመረብ መግቢያ



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

## ስለ በይነመረብ መግቢያ

ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች

## ስለ በይነመረብ መግቢያ

# «አመሰግናለሁ» እና ስልጠና መዝጋት

**ስልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞችዎን እንኳን ደስ አላችሁ ይበሏቸው እንዲሁም የምስክር ወረቀቶችን እንደ ሽልማት ይስጧቸው።**

## ሰልጣኞቹን ያመስግኑ

- **ይጠይቁ፦** «እነዚህን የተደራሽነት ባህሪያት ለመጠቀም በራስ መተማመን ይሰማዎታል?» ወይም «ስልክዎን ለመጠቀም በራስ መተማመን ይሰማዎታል?»
- ለጊዜያቸው፣ ለአስተዋጿቸው እና በስልጠናው ውስጥ ለመሳተፋቸው **ሰልጣኞችዎን ያመስግኑ**።

## የመማሪያ መጽሃፎቹን ይስጧቸው

- አስቀድመው ካልሰጧቸው የስልጠናውን **የመማሪያ ጽሁፎች ለሰልጣኞችዎ ይስጧቸው**።
- እነዚህም «ትርጓሜዎች»ን፣ «በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች»ን፣ «የዳታ ወጪዎች»ን፣ «ጤናማ የበይነመረብ አጠቃቀም»ን እና የበይነመረብ ፖስተሮች መግቢያን ያካትታሉ።







## የመዝጊያ ሥነ ሥርዓት ያካሂዱ

- ለእያንዳንዱ ሰልጣኝ የተፈረመበት የምስክር ወረቀት ይስጡ (የምስክር ወረቀት አብነቶች በአጋዥ ስብስቡ ውስጥ ተካትተዋል)።
- እንዲሁም ለአሰልጣኞች ስልጠናውን «እንደ አሰልጣኞች» ስላጠናቀቁ የምስክር ወረቀት መስጠት ይችላሉ።

**ጠቃሚ ምክር፦** የምስክር ወረቀቱን ለመቀበል እና የአሰልጣኙን እጅ ለመጨበጥ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ወደ ክፍሉ ፊት ለፊት እንዲመጡ በመጠየቅ ለሰልጣኞች ይህን የበለጠ ሥነ ሥርዓታዊ ማድረግ ይችላሉ።



# የምስክር ወረቀት

**መሠረታዊ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች**

ስልጠናን አጠናቅቀዋል።

ቀን

የተፈረመ



# የምስክር ወረቀት

**መሠረታዊ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች**

ስልጠናን አጠናቅቀዋል።

ቀን

የተፈረመ